# Press Release

የአሜሪካ ኤምባሲ
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
*2010*/37

For further information, call 011-130-7431
Internet Address: http://ethiopia.usembassy.gov

---

መስከረም 20 ቀን 2003

## የ2012 ዳይቨርሲቲ ቪዛ ሎተሪ መስከረም 25 ቀን 2002 ይጀመራል

***አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ መስከረም 20፣ 2003 --*** የ2012 ዳይቨርሲቲ ቪዛ (DV) ሎተሪ መርኃ ግብር የማመልከቻ ወቅት መጀመሩን የአሜሪካ ኤምባሲ ዛሬ ይፋ አደረገ። የዳይቨርሲቲ ቪዛ ማመልከቻዎችእ.ኤ.አ. ከኦክቶበር 5 እስከ ኖቬምበር 3፣ 2010 (በኢትዮጵያ አቆጣጠር ማክሰኞ ከመስከረም 25 እስከ ጥቅምት 24 ቀን 2003) ተቀባይነት ይኖራቸዋል። አመልካቾች ኤሌክትሮኒክ የዳይቨርሲቲ ቪዛ ምዝገባ ቅጹን (E-DV) በምዝገባው የጊዜ ገደብ ውስጥ በድረ-ገጽ አድራሻ www.dvlottery.state.gov ማግኘት ይችላሉ። የወረቀት ማመልከቻዎች ተቀባይነት የላቸውም። አመልካቾች እስከምዝገባው ወቅት የመጨረሻ ሳምንት ድረስ እንዳይጠብቁ በጥብቅ ይመከራሉ። በዚያን ወቅት የሚፈጠር የማመልከቻዎች መጨናነቅ ድረ-ገፁን ሊያዘገየው ይችላል። ጥቅምት24 ቀን 2003 እኩለ ቀን በኋላ የሚገቡ ማመልከቻዎች ተቀባይነት አይኖራቸውም።

ዓመታዊው የዲቪ መርኃ ግብር ቀላል፣ ነገር ግን ጥብቅ የሆኑትን መመዘኛዎች ለሚያሟሉ ሰዎች ሁሉ ወደ አሜሪካ ለመሄድ የሚያስችል ቪዛ ያስገኝላቸዋል። ማናቸውም የዲቪ ሎተሪ አመልካቾች ቢያንስ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ወይም የዚያ ተመጣጣኝ አልያም ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ ቢያንስ የሦስት ዓመት ስልጠና ወይም የስራ ልምድ በሚጠይቅ የሙያ መስክ ላይ የተግባር ልምድ ያላቸው ሊሆኑ ይገባል። የትምህርት ወይም የሥራ ልምድ መመዘኛውን የማያሟሉ አመልካቾች ከውድድሩ ውጭ ይደረጋሉ።

በኮምፒዩተር በሚከናወን ሎተሪ ዕጣ አወጣጥ ስርዓት የዳይቨርሲቲ ቪዛ ዕድለኞች ይመረጣሉ። ቪዛዎች (በዓለም ዙርያ) ለስድስት ጂኦግራፊያዊ አካባቢዎች የሚከፋፈሉ ሲሆን፣ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ቪዛዎች (የሕዝቦቻቸው) ወደ አሜሪካ የመፍለስ መጠን አነስተኛ ለሆኑባቸው አካባቢዎች (ወይም አገራት) ይደርሳሉ። ባለፉት አምስት አመታት ውስጥ ከ50,000 የሚበልጡ ዜጎቻቸውን ወደ አሜሪካ የላኩ አገራት የዳይቨርሲቲ ቪዛ ዕድል ተጠቃሚ አይሆኑም። በእያንዳንዱ ጂኦግራፊያዊ አካባቢ ያለ አንድ አገር በአንድ ዓመት ውስጥ ከጠቅላላው ዳይቨርሲቲ ቪዛዎች ውስጥ ከ7 በመቶ የበለጠ አያገኝም።

በ2010 የዩናይትድ ስቴትስ በጀት ዓመት፣ (የአሜሪካ) የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ለዳይቨርሲቲ ቪዛ ሎተሪ መርኃ ግብር ከአስራሁለት ሚሊዮን የሚበልጡ ማመልከቻዎችን ተቀብሏል። ከዚያ ውስጥ፣ ከዓለም ዙርያ 100,000 አመልካቾች የዳይቨርሲቲ ቪዛ ሒደት ውስጥ እንዲገቡ ተመርጠዋል። ከእነዚህ ውስጥ 5,200 ያህሉ የኢትዮጵያ ዜጎች ነበሩ። ባለፉት ዓመታት

ሲያደርግ እንደቆየው፣ በኢትዮጵያ የሚገኘዉ የአሜሪካ ኤምባሲ ከ3,600 በላይ ቪዛዎችን ለዲቪ ዕድለኞች ሰጥቷል፡፡

በአሜሪካ ኮንግረስ ልዩ ስልጣን የተፈቀደው የዳይቨርሲቲ ኢሚግራንት ቪዛ መርኃ ግብር፣ በውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት አስተዳዳሪነት፣ በኢሚግሬሽን እና የዜግነት ሕግ፣ በክፍል 203(ሐ) በተደነገገው መሠረት በየዓመቱ ይካሄዳል፡፡ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት የዳይቨርሲቲ ቪዛ ሒደትን ይበልጥ ቀልጣፋና አስተማማኝ ለማድረግ በመሻት እ.ኤ.አ. ከ2005 ጀምሮ ኤሌክትሮኒክ የምዝገባ ሥርዓትን ተግባራዊ አድርጓል፡፡

በሕገ ወጥ መንገድ ወደ አሜሪካ ለመግባት በመሻት ለማጭበርበር የሚቃጡ ወይም ከአንድ በላይ ማመልከቻ የሚያስገቡ ሰዎችን ለይቶ ለማውጣት ልዩ የሆነ ቴክኖሎጂ እና ሌሎች ስልቶች በጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

የ2012 ዳይቨርሲቲ ቪዛ ሎተሪን ካለፉት ዓመታት ለየት የሚያደርገው አመልካቾች ማመልከቻቸው በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ የሚውቁት በኢንተርኔት በመከታተል ብቻ ይሆናል፡፡ የ2012 ዳይቨርሲቲ ቪዛ ሎተሪ ዕድለኞች መመረጣቸውን የሚያውቁበት ብቸኛው መንገድ ለዲቪ 2012 ሲያመለክቱ ድረ-ገጽ ላይ ያገኙትን የማረጋገጫ ቁጥር (Confirmation number) በመ□ቀም የአሜሪካ ውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት የቆንስላ ጉዳዮች ድረ-ገጽን www.dvlottery.state.gov. (E-DV Entry Status Check) በመከታተል ይሆናል፡፡ የአሜሪካ ውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ለቪዛ ዕድለኞች በፖስታ አድራሻቸው ምንም አይነት የማሳወቂያ ደብዳቤ ወይም ኢሜል አይልክም፡፡

የምዝገባ ቅድመ ሁኔታ እና የዲቪ ሎተሪን አስመልክቶ ተደጋግመው የሚጠየቁ ጥቄዎችን በተመለከተ ዝርዝር መረጃዎችን ለማግኘት፣ እባክዎን የዲቪ-2012 ዳይቨርሲቲ ቪዛ ሎተሪ መመሪያዎችን በአሜሪካ ውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት የቆንስላ ጉዳዮች ድረ-ገጽ www.dvlottery.state.gov. ይመልከቱ፡፡ በኢትዮጵያ የቪዛ ሒደትን የተመለከቱ መረጃዎች ለማግኘት በኢትዮጵያ የአሜሪካ ኤምባሲ ድረ-ገጽን www.ethiopia.usembassy.gov. ይጎብኙ፡፡

###